# አቀባባይ ከበርቴ - ተቀባባይ ካድሬ

ታሪኩ አባዳማ የካቲት 2004

እንደ ወያኔው ጠ/ሚኒስትር የፓርላማ ሪፖርት ከሆነ… (ሰሞኑን እንደዘባረቀው ከሆነ ማለት ይሻላል መሰለኝ) ኢትዮጵያ እንደገና አድጋለች። ዕድገቷ የሚለካው ቻይና ለአፍሪቃ ህብረት ጽ/ቤት በገነባችው ፎቅ ርዝመት ወይስ የሚበላ አጥቶ ጠኔ በሚያንገላታው በሚሊዮን የሚቆጠር ዜጋ አሀዝ መጨመር ላይ ይሁን ገና አልተረጋገጠም። ሰውየው የሚጠቀምበት የዕድገት መለኪያ ሚዛኑ ጭምር የተሰራው ቻይና (made in China) ከሆነ ጠ/ሚኒስትሩ ምን ማለቱ እንደሆነ ይገባናል - የምጣኔ ሀብት ሊቃውንት በቀመሩት አሀዝ ከሆነ ግን "… ቅዝምዝም ወዲያ" ብለን መተው ነው።

በኑሮ ውድነት እየማቀቀ ያለው አዲስአበቤ በበኩሉ ያንኑ ቻይና ሰራሽ ፎቅ ሽቅብ እያየ በባይተዋርነት… 'ይኼ ደግሞ የየትኛው ጄነራል ቤት ይሆን?' በሚል አግራሞት የተዋጠበት ሰሞን ይመስለኛል…

በያቅጣጫው የሚነገረው ጄነራሎች ስለ ገነቡት ፎቅ ሆኗል። እነ ባጫ ደበሌ ሜዳ ያጣበበ ረጃጅም ፎቅ በመገንባት ከጠ/ሚኒስትሩ እጅ የአልሚነት ሽልማት ለመቀበል እየተፎካከሩ ይመስላል። መደበኛ ጦር ትምህርት ቤት ገብቶ የማያውቅ የወያኔ ጄኔራል ትከሻው ላይ አንበሳ ጭኖ ፎቅ ቤት በማስገንባት ውድድር ላይ መሆኑን ከሰሞኑ ያየነው ፎቶ ዘገባ ምስክር ነው።

ያኔ 'ተራሮችን ያንቀጠቀጠው' ታጋይ ሜዳዎችን በፎቅ እያንቆጠቆጠ ነው… በአልሚ ታጋይ ጄነራሎች።

በወያኔ አገዛዝ ዘመን ወታደራዊም ሆነ ሲቪል ሹም ለመሆን ምንም አይነት መደበኛ ትምህርት ማግኘት አይጠይቅም። ጠ/ሚኒስትሩ አንድ ወቅት ላይ እንዳረጋገጠው 'ለፓርቲ ታማኝ ከሆነ ማይም እንኳ ቢሆን በሚኒስትርነት ሊሾም ይችላል…' ብሏል። እንደ እውነቱ ከሆነ የወያኔን ስርዓት ሹማምንት ብቃት ለመለካት ከተፈለገ ከዋናው ከቁንጮው ከጠ/ሚኒስትሩ ብትጀምሩ ሰውየው ከዛሬ ሀያ አመታት በፊት ወደ ፕሬዘዳንትነት ወንበር ከመውጣቱ በፊት የነበረው የሥራ ልምድ ወይንም መደበኛ የአስተዳደር ወይንም አመራር እውቀት ምን ነበር? ባንክ ዘረፋ ፣ ፓርቲ ካድሬ ምልመላ ፣ ተቀናቃኝ በሾኬ ጠለፋ … እያለ ይቀጥላል። መለስ ዜናዊ 'ሚኒስትር ለመሆን ትምህርት ወይንም አስተዳደር ልምድ አይጠይቅም' ብሎ ሲናገር ስለ እራሱ ጭምር እውነቱን እየነገረን ስለመሆኑ ምን ያህል እንዳጤን አላውቅም።

'የአሳ ግማቱ ከወደ አናቱ' ነው ያሉት አበው? ቀጥታ ከጫካ ወደ ዕድሜ ልክ ፕሬዘዳንት (ጠ/ሚኒስትር)።

ለግዜው ግን ኢኮኖሚው አለም በቃኝ በተገነባው (የቻይና መባ) ሀያ አራት ፎቅ ሽቅብ ሲመነደግ ጋምቤላ እና ደቡብ ኢትዮጵያ ደግሞ መሬታቸውን ለህንድ እና አረብ 'ገበሬዎች' ለቀው እንዲነሱ በተገደዱ በመቶሺ ተፈናቃይ ዜጎች ቁጥር እንዲሁም የአለም አቀፍ ረድዔት እጅ አይተው በሚያድሩ ሚሊየን ተረጂ ዜጎች ብዛት እጅግ አድጋለች - እጥፍ ድርብ ዕድገት ይሏል ይህ ነው።

በወያኔ ዘመን አዲስ የተፈጠረው የአንድ ጀምበር ቱጃሮች ጥሪት እና ጉልበት እደነደነ ነው። በወያኔ ዘመን ሚኒስትር ለመሆን ብቻ ሳይሆን ከበርቴ ለመሆን የሥርዓቱ ታማኝ መሆን ግድ ይላል።

ለስድሳ ስድስት አብዮት ምስጋና ይግባውና የመደብ ትንተና ሀሁ ስንቆጥር ግምሽ ዕድሜያችንን አሳልፈናል - የመደብ ትንተና መዝገብ ውስጥ ከነበሩት መካከል ታዲያ 'አቀባባይ ከበርቴ' በእንግሊዝኛው ትርጉም (Comprador bourgeois) ይሰኝ የነበረው እንዱ መሆኑ ትዝ ይላችሁዋል። ተንታኙ ሲገልጠው ታዲያ አገር በቀል ከበርቴዎች በተለይም ከድንበር ዘለል ባለሀብቶች ጋር የተቆራኙ ፣ ከግዙፍ ብሔራዊ ኮርፖሮሽኖች ጋር የተመሳጠሩ ፣ የባንክ ባለሀብቶች (አራጣ አበዳሪዎች) ብሎም በወታደራዊ ኢንዱስትሪ ውጤቶች ድለላ ላይ የተሰማሩትን በሙሉ… የሚያጠቃልል ነው። አቀባባይ ከበርቴዎች እንደ ትርጉሙ አግባብ ከሆነ የጮሌ ቢዝነስ ሰዎችን አቋራጭ እና ፈጣን ሀብት የማፍራት ቅልጥፍና እና ባህሪ ገላጭ ነው። በአገራችን ዛሬ የተፈጠረውን አቀባባይ ከበርቴ (ካድሬዎች) መደብ ለመግለፅ ግን ሌላ አዲስ ትንተና ይጠይቃል።

የፖለቲካ ስልጣን እና ገዢ ፓርቲ ተገን አድርጎ ሀብት መሰብሰብ እና ከበርቴ መሆን ከአቀባባይ ከበርቴ ተራ ሊያሰልፍ ቢችልም አፈጣጠሩ ግን ወትሮ ከምናውቀው አይነት (Comprador bourgeois) እጅጉን ይለያል። የካድሬ ከበርቴ ሀብት ባንድ ጀምበር እንደተፈጠረ ሁሉ ባንድ ቀን 'የፓርቲ ግምገማ' ሊወስድብህ ይችላል። ታማኝነትህ ብቻ ሳይሆን ለጌቶች እና ለፓርቲያቸው በስልጣን መቆየት የምታደርገው አስተዋፅኦ ሚዛን ላይ ይቀመጣል። ጎሳህ ፣ ብሔረሰብ ሀይማኖት ወይንም ክልል እንደ ሁኔታው… ጠቀሜታህ ይለካል።

*እነ ባጫ ደበሌ ጦር ሜዳ የተማረኩ አስር አለቆች ነበሩ - እና ስማቸውን ኦሮማዊ አድርገው 'ተጨቁኖ ቆየ' የተባለውን ኦሮሞ ህዝብ በመወከል ፓርቲ ተመስርቶላቸዋል። በተመሰረተላቸው ፓርቲ ጥላ ስር ሆነው ተደንግጎ በተሰጣቸው ክልል ገደብ የለሽ ዘረፋ ያካሂዳሉ/ይደረጃሉ… የታማኝ ካድሬ መንጋ ያደራጃሉ።*

*በወያኔ አገዛዝ ዘመን ባለ ሀብት ሆኖ ለመቀጠል ታማኝነት ምን ድርሻ እንዳለው ለማረጋገጥ ሌላው ጥሩ ምሳሌ ሼክ አላሙዲ ነው። የገዛ አዱኛውን ይዞ አገር ውስጥ የገባው ሼክ አላሙዲ በሀብት ላይ ሀብት ለማደርጀት የግድ የወያኔ ታማኝነቱን በተለያየ መንገድ አረጋግጦ ማሳየት አለበት። ሥርዓቱ ይህን ሆኖ እንዲገኝ ያስገድደዋል። በታማኝነቱ ባገኘው ያልተገደበ ፈቃድ ደግሞ ያሻውን መሬት አሳጥሮ ሲሻው ፀሀይ ያስመተዋል ወይንም ያተርፈኛል ያለውን ነገር ሁሉ ያመርተብታል - ወርቁን ፣ ፋብሪካውን ፣ እርሻውን ምኑ ቅጡ… ታማኝ መሆኑን በየመድረኩ ማደስ 'በኢሕአዴግ ፀበል ተጠምቄያለሁ… '።*

*ታማኙ ቱጃር አላሙዲ ከኢትዮጵያ ሰማይ በታች ያሻውን የማድረግ መብት ተጎናፅፏል። በበኩሌ ሰውየው አቅሙ እስካለው ድረስ በህግ አግባብ መሰረት ቢንቀሳቀስ ቅንጣት ቅሬታ ያለው ዜጋ አለ ብዬ አልገምትም። ጉዳዩ ግን እንደዚያ አይደለም - ፖለቲካ ስልጣን ተገን አድርጎ ሀብት ማግበስበስ መዘዝ እንዳለው መረዳት የማይችል አላሙዲንን የሚያክል ባለሀበት ከብልጣብልጦቹ አቀባበይ ከበርቴዎች ተራ ውስጥ ሊመደብ መብቃቱን እጠራጠራለሁ። አላሙዲን* (Comprador bourgeois) *ለመባል የሚጎድለው ነገር አለ።*

*ባንድ ጀምበር ሚሊየነር ሆነው ፎቅ ገንቢ የሆኑት ጄነራሎች እና አላሙዲን የመሳሰሉ የወያኔ ዘመን ባለሀብቶች በጥቅሉ* (Comprador bourgeois) *ከምንላቸው ይልቅ* (Comrade bourgeois) *ጓድ ከበርቴዎች ብንላቸው የቃሉ አግባብ የተሻለ ገላጭነት አለው ብዬ ገምታለሁ።*

*ለነ ባጫ ደበሌ ጄነራል የመሆን ፋይዳው አገር ለመጠበቅ እና ዳር ድንበርን ለማስከበር ወታደራዊ ጥበብ መቅሰም እና ብቁ ሆኖ መገኘት ሳይሆን የጅምላ ትርፍ ምንጭ የሆነው ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ብሎም የዚህ ስርዓት ቁንጮ እንዳይታወክ በንቃት መጠበቁ ላይ ነው። እነሱ ሜዳውን በፎቅ ሲያጣብቡ ስርዓቱ ደግሞ ዕድሜውን ለማቆየት ተተኪ ካድሬዎችን ይመለምላል ፣ ያሰለጥናል ፣ ያጠምቃል ፣ ይሾማል - ፎቅ መስሪያ ረብጣ ያስታቅፋል። ኤፈርት ፣ ትግራይ ልማት አማራ ልማት እየተባለ ኦዲት የማይፈትሸው ጭፍን ዘረፋ በዘመቻ ይካሄዳል። በጫካ ህግ እየተመራ ያለ ኢኮኖሚ ይዘቱ ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም።*

*ወያኔ የሚደነፋበት ኢኮኖሚው አደገ ማለት ከዚህ ውጭ ከሆነ የሚባለውን ለመስማት ዝግጁ ነኝ። እስከ ዛሬ ድረስ በገሀድ እነደታየው ከሆነ ግን ሀቁ በአጭር አገላለፅ ይህን ይመስላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሳይጠቀስ መታለፍ ያለበት አቢይ ቁምነገር ቢኖር - የሥርዓቱ ዕድሜ እንዳያጥር ፣ በአቀባባይ ጓድ ከበርቴዎች የተገነባው የኢኮኖሚ ዕድገት ሂደቱ እንዳይታወክ የመተካካት ስልት መሳ ለመሳ የተቀየሰ መሆኑን ነው - ሥልጣን ለመቀባባል… ቅብብሎሽ።*

*ማን ለማን እንደሚያቀብል እናማን እንደሚቀባበሉ በግል ደረጃ መናገር ቢቸግርም ቭላድሚር ፑቲን ለዲሚትሪ ሜድቬዴቭ ከዚያ ሜድቬዴቭ መልሶ ለፑቲን አይነት ቅብብሎሽ እንደሚሆን ግን ከወዲሁ መተንበይ አያስቸግርም። ጠ/ሚኒስትሩ 'ፓርቲዬ ይፈልገኛል' ካሉ ደግሞ ቅብብሎሹ በይደር ይታለፋል ወይንም ሌላ ቅርፅ ይዞ እንዲከናወን ይደረጋል - በቅብብሎሽ እና አቀባባይ ካድሬዎች።*

*እንዲህ አይነት አስገራሚ ድራማ በሚሰራባት አገር ከሰማንያ ሚሊየን ህዝብ በላይ ይኖርባታል። ሰማንያ ሚሊዮን ዜጋ የአንድ ፈላጭ ቆራጭ ግለሰብ እና ጎጠኛ ፓርቲ ማላገጫ ሆኖ ሀያ ዓመታት ማለፋቸው እጅግ አድርጎ የሚደንቅ ክስተት ነው። እኛ እንደሌላው አገር ህዝብ ለግል ስብዕናችን ፣ ለአገራችን እና ለወገናችን ክብር እና ማንነት የማንቆረቆር ሆነን ነው ወይንስ - የፖለቲካ ንቃት ይጎድለናል?*

*ንቃት?*

*የፖለቲካ ንቃት ማለት በአገር ወስጥ ስላለው አገዛዝ ተፈጥሮ ተገቢ ግንዛቤ ማዳበር ማለት ነው።*

*ስለ ማህበራዊ ፍትህ መስፈን ፣ ስለ ብሔራዊ ክብር ፣ ስለ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ፣ ስለ ሰብአዊ መብቶች ጥበቃ እና መረጋገጥ ብሎም ስለ ህግ የበላይነት መረጋገጥ እና መፅናት መሬት ላይ ያለውን እውነት መገንዘብ - የማወራው ስለ ዛሬይቱ ኢትዮጵያና ወያኔ ነው እናም እውነቱ ሙስና ፣ ሽፍጥ ፣ ጎጠኝነት ፣ ባርነት ፣ አፈና ፣ እስር ፣ ስደት ፣ ሞት…*

*እስከ ዛሬ ያልነቃችሁ ንቁ - ትናንት የነቃችሁ ደግሞ ዛሬ ሌላ ቀን ነው እንደገና ንቁ።*